# ማኅበረ ቅዱሳን ክርስቲያናዊ ድርጅት በመሆኑ ከወያኔ ጥቃት ራሱን የመከላከል እርምጃ መውሰድ አይችልም! ያለው ማን ነው?

መሰንበቻውን "ማኅበረ ቅዱሳን ሊፈርስ ወይም ሊዘጋ ነው!" የሚል ወሬ ከዚህም ከዚያም ሲሰማ ንቄ አልፌው ነበረ። ይሄንን ነገር ወያኔ እርምጃውን ለመውሰድ ስለተዘጋጀ የሕዝቡን የልብ ትርታ ለማዳመጥ ሆን ብሎ እያስወራው እንደሆነ የገባኝ ስለዚህ ጉዳይ ከዓመት በፊት ዳንኤል ክብረትም ጽፎ መርዙን የረጨበትን ጽሑፍ እንደ አዲስ ሲዘዋወር ባየሁ ጊዜ ነው።

ወያኔ ማኅበረ ቅዱሳንን ለምን ማፍረስ እንደፈለገ ከዓመታት በፊት ወያኔ ማኅበሩን የማፍረስ ዛቻ ባሰማበት ወቅት በተከታታይ በጻፍኳቸው ጽሑፎች በዝርዝር የጻፍኩበት ጉዳይ በመሆኑ እዚህ ላይ አልደግመውም። በአጭሩ መግለጽ ካስፈለገ ግን ወያኔ ማኅበረ ቅዱሳንን አንባገነናዊና ሕገወጥ በሆነ መንገድ ሊያፈርስ የፈለገበት ምክንያት "አከርካሪዋን ሰብሬዋለሁ!" በሚላት በዚህች ሀገር ባለአደራ በቅድስት ቤተክርስቲያንና በሀገራችን ላይ ላለው ሰይጣናዊ የጥፋት ተልእኮ  ትልቅ እንቅፋት ሆኖ እያደናቀፈ አላንቀሳቅስ ስላለው፣ እንደ ዜጋ ለሀገር እንዲሁም እንደ ክርስቲያን ለቤተክርስቲያን በመቆርቆሩ፣ ጥብቅና በመቆሙ ነው በሌላ በምንም አይደለም።

ያውም እኮ ማኅበረ ቅዱሳን በወያኔ ከባድ ጫናና ወከባ ምክንያት አባቶቻችን ሐዋርያቱ፣ ሠማዕታቱና መነኮሳቱ ባስቀመጡለት አሰረ ፍኖት ወይም አርአያነት እንደ ክርስቲያናዊና የሀገር ጉዳይ እንደሚገደው ኢትዮጵያዊ ሲቪክ (ሕዝባዊ) ድርጅት ወንጌልን በሚሰብክበት ወቅት "አትስረቅ!" ይላልና ቃሉ የሰረቁ ወይም የዘረፉ ወይም ሙሰኛ ወይም እምነት ያጎደሉ ባለሥልጣናት ለፍርድ ይቅረቡ! ፣ "አትግደል!" ይላልና ቃሉ ዜጎችን ያለፍርድ በግፍ የገደሉ ባለሥልጣናት ለፍርድ ይቅረቡ! ፣ ድሀ ተበደለ ፍርድ ተጓደለ ወዘተረፈ. እያለ እንደ ክርስቲያናዊ ድርጅት ማድረግ ያለበትን ሳያደርግ፣ ዓለሙን መስበክ ያለበትን ሳይሰብክ፣ መንቀሳቀስ እንዳለበት ሳይንቀሳቀስ እኮነው ወያኔ እንዲህ ማኅበረ ቅዱሳንን ጥምድ አድርጎ የያዘው። በዚህ ጽሑፌ መዳሰስ የፈለኩት ጉዳይ ማኅበረ ቅዱሳን እራሱን ከግፈኛ ጥቃት የመከላከያ መንገድ ያለው ስለመሆኑ እናያለን።

ወያኔ እንደ ዳንኤል ክብረት ባሉ ካድሬዎቹ (ወስዋሾቹ) ቀደም ሲል ጀምሮ ማኅበረ ቅዱሳን በአመራሮቹ ድክመት የተነሣ ሊሠራ ያልቻለ እንደሆነ፣ በፍርሐት ቆፈን ተቀፍድዶ የተያዘ እንደሆነ ደጋግሞ በማስተጋባት ቢፈርስም እንዳንቆጭ ለማድረግ ጥረት ቢያደርግም፤ እንደገና ደግሞ እዚያው ማኅበረ ቅዱሳንን በከሰሰበት በወነጀለበት ስም ባጠፋበት ጽሑፉ ላይ "ማኅበሩን የሚመራው የማይታይ የማይታወቅ ስውር አካል አለ!" በማለት ወያኔ በማኅበረ ቅዱሳን ላይ የሚወስደውን ኢፍትሐዊና ሕገወጥ እርምጃ ተገቢነት ያለው መስሎ እንዲታይ እንዲታሰብ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ማኅበረ ቅዱሳን በወያኔ ከባድ ጫናና ወከባ ምክንያት የፍላጎቱን ያህል፣ የአቅሙን ያህል፣ መሥራት ያለበትን ያህል፣ የሚጠበቅበትን ያህል መንቀሳቀስ እንዳልቻለ ከማናችንም የተሠወረ አይደለም። ማኅበረ ቅዱሳን እንዲህ ተኮድኩዶ የሚሠራው ሥራም ቢሆን ግን ወያኔን ምን ያህል እረፍት ነስቶት እንዳለ የምትመለከቱት ነው።

ወያኔ አሁን ደግሞ በካድሬው (በወስዋሹ) በዚሁ ቆሻሻ ተኩላ ዳንኤል ክብረት በኩል "ማኅበረ ቅዱሳን ግዘፋዊ ኑባሬ እንዳይኖረው ቢደረግም (ቢዘጋ ቢፈርስ ማለቱ ነው) እንደ ሠማዕታት በሥራው ዘለዓለማዊ መሆን ይችላልና ክርስትና የኃይል አጸፋ የሚመልስበት መንገድ ስለሌለው እግዚአብሔር የሚያደርገውን ከመጠበቅ ውጭ ምንም ልናደርግ የምንችልበት አማራጭ የለም! ግማሽ ክ/ዘ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ማኅበሩን በማፍረሳቸው ተጸጽተው ይመልሱታል!" የሚል አብጋኝና ሸፍጠኛ ጽሑፍ በማሠራጨት ወያኔ ገና ሐምሳ ዓመት የሚቆይ መሆኑን ሕዝቡ አምኖ እንዲቀበል ለማድረግ በመሞከር ተስፋ ቆርጠን ወያኔ የሚለንን እየተቀበልን እንድንቀመጥ፣ የማኅበረ ቅዱሳንን መፍረስም በጸጋ እንድንቀበል ለማድረግ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

በተለያዩ ምክንያቶች ለክርስትና ሕግጋት የጠራና ትክክለኛ ግንዛቤ እየታጣ በመጣበት በዚህ ዘመን "ማኅበረ ቅዱሳን ክርስቲያናዊ ማኅበር እንደመሆኑ ለሚደርስበት ክፉ ጥቃት ክፉ አጸፋ ያለመመለስ ግዴታ አለበት!" የሚለው የተሳሳተና ክርስቲያናዊ ያልሆነ አስተሳሰብ ወያኔን የልብ ልብ ሳይሰጠው አልቀረም፡፡

እንዲያው ግን ለመሆኑ "ክርስትና በየጊዜው የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች እንዴት እያለፈ ነው ለዚህ የደረሰው?" ብለን እራሳችንን ጠይቀን እናውቃለን? ጠይቀን ካወቅንስ ለዚህ ጥያቄያችን ምን ምላሽ አገኘንለት? "መጽሐፉ እንደሚያዘው ሊያጠፉት ለመጡት ሁሉ አንገቱን እየሰጠ ነው ለዚህ የደረሰው!" የሚል ምላሽ ከሆነ ያገኛቹሀት ፍጹም መሳሳታቹሀን ልነግራቹ እወዳለሁ፡፡ ታሪካችንን አገላብጣቹ ብታዩት እውነታው ይህ የገመታቹሀት አለመሆኑን በሚገባ ያረጋግጥላቹሀል፡፡ በዮዲት ጉዲት ዘመንም በሉት፣ በግራኝ አሕመድ ዘመንም በሉት፣ በፋሽስት ጣልያን ዘመንም በሉት በሌላም ገፍቶ የመጣብንን ጠላት በመዋጋታችን የእግዚአብሔር ረድኤት በግልጽ እየታየም ሁሉ አሸንፈን ሃይማኖታችንን ጠብቀን አቆየን እንጅ ዮዲት ጉዲት ክርስትናቹሀን ጥላቹሀ አይሁድ ሁኑ እንዳለችን፣ ግራኝ አሕመድ ክርስትናቹሀን ጥላቹሀ ስለሙ እንዳለን፣ ፋሽስት ጣልያን ክርስትናቹሀን ጥላቹሀ ኮትልኩ እንዳለን መዋጋታችንን ትተን እሽ እያልን የሚሉንን ብናደርግ ኖሮ ዛሬ ክርስትናና ማንነታችን ከዚህች ሀገር ገና ድሮ ደብዛው በጠፋ ነበር፡፡

በሌሎች ሀገራት ለምሳሌ በአራተኛው መቶ ክ/ዘ መለካውያኑ መነኮሳቶቻቸው በፈጠሩት ክፍተት ለኑፋቄ ተዳርጋ ከትክክለኛው የክርስትና መንገድ መስመር ከመሳቷ በፊት ክርስትና ጥብቅ መሠረት የነበረባትን የጥንታዊት ሮምን ተሞክሮ ያየን እንደሆነም ከእኛ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህች ሀገር በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ በክርስቲያንነታቸው ምክንያት የመጣባቸውን ፈተና እንዴት እንደተወጡትና ምን እንደተፈጠረ ጠቋሚያቹሀ ልለፍ፡፡

በዚህች ሀገር በሮም አረማውያን ክርስትናን ለማጥፋት በተነሡ ጊዜ አረማውያንንና ከሀድያንን በሰይፍ እየቀሉ የፈጁና በሠማዕትነት አልፈው በእግዚአብሔር መንግሥት ለታላቅ ክብር የበቁ ቤተክርስቲያን የቅድስና ክብር የሰጠቻቸውን በርካታ ቅዱሳን ሠማዕታትን እናገኛለን፡፡ እነኝህ ምሥራቃውያን ሠማዕታት ወይም ሮማውያን በመባል የሚታወቁት ሠማዕታት ሠማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዮስ፣ ሠማዕቱ ቅዱስ ፋሲለደስ፣ ሠማዕቱ ቅዱስ ገላውዴዎስ፣ ሠማዕቱ ቅዱስ አውሳብዮስ፣ ሠማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር፣ ሠማዕቱ ቅዱስ ዮስጦስ፣ ሠማዕቱ ቅዱስ መቃርስ፣ ሠማዕቱ ቅዱስ ቴዎድሮስ፣ ሠማዕቱ ቅዱስ ጊጋር ወዘተረፈ. የሚባሉ የጦር መሪዎች ናቸው፡፡ ዝርዝሩን ከየገድሎቻቸው ተመልከቱት፡፡ በነገራችን ላይ እነኝህ ቅዱሳን ሠማዕታት ቅዱስነታቸው ለእኛ ብቻ አይደለም ለካቶሊኮችም ጭምር ቅዱሳን ናቸው፡፡

ይህ የእነኝህ ቅዱሳን ሠማዕታት የቤተክርስቲያን አርበኞች ተግባር ከክርስትና ጋር የሚቃረን የሚመስለን ቂሎች አንጠፋም፡፡ ለእነኝህ የዋሀን "በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና!" ሮሜ. 13፥4 የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ልብ ይሉት ዘንድ እመክራለሁ፡፡

ልብ በሉ! ከገድሎቻቸው በግልጽ እንደምንረዳው ለሠማዕቱ ቅዱስ ቴዎድሮስ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል፣ ለሠማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ድል የሚነሱበትን ሰማያዊ ሠይፍ ሰጥተዋቸው አረማውያንንና ከሀድያን ጠላቶቻቸውን እንዲፈጁ ከማድረጋቸው ከእነኝህ የቤተክርስቲያን ቅዱሳን ሠማዕታት ተጋድሎ የምንማረው ቁምነገር ቢኖር ክርስትና አልፎ አይሔድም፣ በጉልበቱ የማንንም ሀብት ንብረት ሙብት አይነጥቅም፡፡ በግፍ ከመጡበት ግን እራሱን የመከላከል ነጻነት ያለው እንጅ እንደመሥዋዕት በግ በጅምላ እየተነዱ የሚፈጁበት የሚያልቁበት የቂሎች መንገድ አለመሆኑን ነው! "ቀኝህን ሲመታህ ግራህን አዙርለት፣ መነናጸፊያህን ቢወስድብህ እጀጠባብህን ጨምርለት፣ ጠላትህን ውደድ ...!" የክርስትና ሕግጋት መቸ? የት? እና ለማን? ተብሎ ቦታና ጊዜ የሚመረጥላቸው ሕግጋት መሆናቸውን ጠንቅቀን ካላወቅን ክርስትና ፈጽሞ አልገባንም ብቻ ሳይሆን እራሳችንንም አብዝተን እያቄልንና እየዋሸን መሆናችንን ልናውቅ ይገባል!!!

በዛሬ ዘመን እንደምታዩት ለሆዳችን፣ ለጥቅማችን፣ ለሥጋችን አደርንና ሠማዕት የሚሆን ሰው ጠፋ እንጅ በቤተክርስቲያን ታሪክ እንደዚህ ዘመን የዘመነ ሠማዕታት ዘመን ኖሮ አያውቅም፡፡ ወያኔ "አከርካሪዋን ሰብሬዋለሁ!" ብሎ ለመፎከር እስከሚችል እንደ እነ አባ ጳውሎስ አባ ማትያስና በስሮቻቸው ያሉ አገልጋዮቹን አስርጎ አስገብቶ የሚታይና የማይታይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ ይህችን ቤተክርስቲያን እንዳትሆን አድርጎ ሲጫወትባት፣ መንጋዋን በመናፍቃን ሲያስበላባት፣ ዶግማ ቀኖናዋን ሲቆነጻጽልባት፣ ሀብት ንብረቷን ሲዘርፍባት ወዘተረፈ. ሰምተን እንዳልሰማን፣ ዓይተን እንዳላየን አሳለፍን እንጅ እንደ እናት አባቶቻችን "እንቢ ለሃይማኖቴ! እምቢ ለቤተክርስቲያኔ!" ብለን ቅድስት ቤተክርስቲያንን፣ ሃይማኖታችንን ለመታደግ ፊት ተሰላፊ ሆነን ሠማዕት እስከመሆን ድረስ አልታገልንም፣ አልተዋጋንም አልተጋደልንም፡፡

አንድ ጥርጥር የሌለው ነገር አለ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ተዘጋ ህልውናውን አጣ ማለት ይህችን ቤተክርስቲያን በአፍ ጢሟ ደፍተው ቀበሯት ማለት እንደሆነ እያንዳንድሽ ካላበልሽ በስተቀር ልቡናሽ ያውቀዋል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ባይኖር ኖሮ እንደ መናፍቃንና ወያኔ ከፍተኛ የጥምረት ጥረት ቢሆን እስከአሁን ድረስ ይህች ቤተክርስቲያን ታሪክ ሆና ቀርታ ነበር፡፡ ይሄንን ልብ ያላለ ሰው ቢኖር ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖሩ ወይም ማስተዋል የሚችል ሰው ለመሆኑ እጠራጠራለሁ፡፡

እስኪ አንድ ነገር ላሳስባቹህ! ወያኔን "ማኅበረ ቅዱሳንን ለማፍረስ የፈለክበት ምክንያት በየትኛው የሀገሪቱ ሕግ ነው መብት እንጅ ወንጀል ሆኖ የቀረበው? ፣ እንዴትስ ሆኖ ነው ጠባብ ቡድኖችን እንጅ ሀገሪቱንና ሕዝቧን የሚጎዳው?" ብላቹህ ጠይቁት እስኪ?

ወያኔ ልብና ሕጋዊነት ይዞ እራሱን ግልጽ አድርጎ ተጠያቂነት ባለው መንገድ በመቅረብ በፍጹም በፍጹም ማኅበረ ቅዱሳንን ሊሞግት አይችልም፡፡ ማኅበረ ቅዱሳንን ለመዝጋት የሚያበቃ በማኅበረ ቅዱሳን ላይ "እንዲህ... ስላደረጉ ነው የማፈርሳቸው!" ብሎ ሊጠቅሰው የሚችል አንድም ወንጀል ኖሮት አያውቅም፡፡ ወያኔ ማኅበረ ቅዱሳንን ለመዝጋት እየተጣደፈ ያለው ማኅበረ ቅዱሳንን ፍርድ ቤት ከሶ የፍትሕ አካሉ እንዲዘጋው ስለወሰነለትም አይደለም፡፡ በሕጋዊ መንገድ ማኅበረ ቅዱሳንን ለማዘጋት ፈጽሞ እንደማይችልና ማኅበሩም የሀገሩቱ ሕግ እንዲሠራ መብቱ መሆኑን ካረጋገጠለት ተግባር ውጭ ሊያስከስሰው የሚችል ወንጀል እንደሌለበት ስለሚያውቅ ነው ወንበዴው ወያኔ በሕጋዊ መንገድ ሳይሆን ሕገወጥ በሆነ አንባገነናዊ የውንብድና መንገድ ሊዘጋው ሊያፈርሰው አቆብቁቦ ያለው፡፡

እሸ እኛ ታዲያ ይህ ሁሉ ሲሆን እጅና እግራችንን አጣምረን ነው ዝም ጭጭ ብለን የምንመለከተው ወይንስ "እምቢ ለሃይማኖቴ! እምቢ ለቤተክርስቲያኔ!" ብለን እንደ ሠማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዮስ፣ እንደ ሠማዕቱ ቅዱስ ፋሲለደስ፣ እንደ ሠማዕቱ ቅዱስ ቴዎድሮስ፣ እንደ ሠማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር፣ እንደ ሠማዕቱ ቅዱስ ገላውዴዎስ ወዘተረፈ. ሠይፋችንን፣ አካፋ ዶማችንን፣ ድንጋይ በትራችንን፣ ቦምብ ያለህ ቦንብህን፣ ሽጉጥ ያለህ ሽጉጥህን፣ መሣሪያ ያለህ መሣሪያህን፣ ቢላ ጩቤ በርበሬህን ወዘተረፈ. ይዘን ሴት ወንዱ ወጣት አዛውንቱ ከካህን በስተቀር (ካህን ሰው እንዲገድል ስላልተፈቀደለት ነው፡፡ ከመግደል በመለስ ባለው ጉዳይ ግን ልክ አድዋ ላይ እንደዘመቱት ካህናት አባቶቻችን መሳተፍ ይኖርባቸዋል) ሁሉም ክርስቲያን በመውጣት የአጋንንቱን የወያኔን ጭፍራ በመፍጀትና ሠማዕት በመሆን ቤተክርስቲያናችንን ሃይማኖታችንን እንታደጋለን???

ወገን ሆይ! "አዎ እንዴታ!" ያልክ እንደሆነ ዘርህ ይባረክ! ከመልካሙ ቀን ያድርስህ! ከፉውን ዘመን ያሻግርህ! በጠላቶችህ ላይ ያሠልጥንህ! እንደ ብረት ያጠንክርህ! እንደ አለት ያጽናህ! ትንሣኤህን ያሳይህ! የቅዱሳን ሠማዕታት እናት አባቶችህ ልጅ በመሆንህም ኩራ! ፡፡ "አይ አይደለም! ምን ልብና ወኔ አለኝና!" ያልክ እንደሆነ ግን ዘርህ አይባረክ! የዘራኸው አይብቀል! ከድህነትህ አያውጣህ! ከባርነትህ አያላቅህ! እንደተሠበርክ እንደተንበረከክ ያኑርህ! ጨለማው አይንጋልህ! እርጉም ሁን!!!

ድል ለቤተክርስቲያን!!! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com